የብሔራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 564/2013

National Science and Technology Research Council's Research Support Guide (Directive No. 564/2013)

የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
Ministry of Science and Technology

ጥቅምት 1፥ 2007

1. መግቢያ

በአንድ ሃገር ቴክኖሎጂዎችን የመማር፣ የማስገባት፣ የማላመድና የመጠቀም እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የተጠናከረ የምርምር ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ በሃገራችን ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም የምርምር ስራ የሃገሪቱን ዋና ዋና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈታ፣ ለሃገራችን የልማት ግቦች መሳካት አስተዋፅዖ የሚያደርግና እዛው ሳለ የቴክኖሎጂ ፍላጎትን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ሀገራዊው የምርምር ስርዓት ውጤታማ የሆኑ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን በማፈላለግ፣ በመማር፣ በማላመድና በመጠቀም ረገድ የሃገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

አሁን በሀገራችን ባሉት የምርምር ተቋማትም ሆነ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄዱ ምርምሮች ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት እንዲኖራቸው የማድረግና ተመራማሪዎቻችንም በዚህ ቅኝት ውስጥ እንዲገቡና ለሀገራዊ የልማት አጀንዳዎቻችን ስኬት የማይተካ ሚናቸውን እንዲወጡ የማድረግ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡ በመንግስት የሚሰጡ የምርምር ድጋፎችም ይህንን እና ይህንን ብቻ እንዲያሳኩ በሚያስችላቸው መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በተበታተነ መልኩ እየተካሄዱ ያሉና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚፈስባቸው የምርምር ስራዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲመሩና አላስፈላጊ ድግግሞሽና የሃብት ብክነትንም ለማስቀረት፣ ብሎም የሀገሪቱን የምርምር አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት፣ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በየዘርፉ የምርምር ቅደም ተከተሎችን የሚያወጣ፣ በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱት ምርምሮች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚገመግም፣ በየዓመቱ የሚካሄዱትን ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም አዳዲስ የምርምር መስኮችን የሚለይና የሚወስን፣ ለምርምር የሚያስፈልግ የበጀት ፍላጎት መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ፣ በምርምር ዙሪያ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤትን የሚያማክር፣ አፈፃፀሙንም የሚከታተልና ፣የሚገመግም፣ የቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች ላይ የሚስተዋሉትን ክፍተቶች በመለየት አዳዲስ የምርምር ተቋማት እንዲቋቋሙ ለብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ምክረ ሐሳብ የሚያቀርብ አካል ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ካውንስል ተቋቁሟል፡፡

በዚህም መሰረት ብሄራዊ ካውንስሉ የተጣለበትን ተግባርና ሃላፊነት ለመወጣት እንዲረዳው ይህ አሰራር መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

2. የ መመሪያው አስፈላጊነት

የሳይንስና ቴክኖሎ... የሬኮርድ ማህደር አገልግሎት አዲስ አበባ

1. ካውንስሉ በብሄራዊ ደረጃ ለሚሰጠው የምርምር ማካሄጃ ድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክቶችን ለማወዳደር የሚያግዝ ግልፅና ዝርዝር መስፈርት ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤
2. ከምርምር ውጤቶች የባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን በአግባቡ ለማስተናገድና ምላሽ ለመስጠት የሚያግዝ በመሆኑ፤
3. የካውንስሉን አሰራርና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት እንደዚሁም የካውንስሉን አባላት ሃላፊነቶች በግልፅ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ናቸው፡፡

ክፍል - አንድ

አጠቃላይ

3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ካውንስል ድጋፍ አሰጣጥ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 564/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

4.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **ሳይንስ ማለት፡-** ነባራዊውን አለም እና የተፈጥሮ ህግጋትንና ክስተቶችን ለማብራራትና ለመገንዘብ የሚያስችለንን እውቀት በምልከታና በሙከራ የምናገኝበት ዘዴ ነው፡፡
2. **ቴክኖሎጂ ማለት** ፡- የአንድን ኅብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል፣ የምርት አመራረትና የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከአጠቃቀም ጋር የተጣመረ ዕውቀት ፣ የድርጊት ጥበብ (Knowhow) ፣የአሠራር ዘዴና ሥርዓት ነው፡፡
3. **ኢኖቬሽን ማለት፡-** የተፈጠረ ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል፣ለነበረ ቴክኖሎጂ አዲስ የጥሬ ዕቃ ምንጭ ወይም አዲስ ገበያ የማስገኘት ወይም በነበረ ቴክኖሎጂ ላይ በማከል ቴክኖሎጂውን የተሻሻለ ፣ የቀለጠፈ ወይም በዚሁ የማሻሻል ሥራ የተነሳ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት ጊዜንና ወጪን የሚቀንስ ወይም ገበያን የሚያሰፋ ቴክኒካዊ የመፍትሄ ሃሳብ ነው፡፡

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

3. **ቴክኖሎጂ ሽግግር ማለት፡-** በሌሎች ወገኖች የተፈጠረና በተግባር የተፈተነ ቴክኖሎጂን ወይም የአሰራር ዘዴን በካፒታልና በኢንተርሚዲየር ዕቃዎች ወይም በሰለጠነ የሰው ኃይል ወይም በቴክኒክና ንግድ መረጃዎች አማካኝነት ወደ ተቀባይ ወገኖች የማስተላለፍ ሂደት ሆኖ ፤ ይህ ሂደት የተሟላ የሚሆነው ከሰጪው/ከአቅራቢው የተላለፈው ዕውቀት ተቀባዩን ተመሳሳይ ምርት ለማምረትና አገልግሎት ለመስጠት ሲያስችለው ነው፡፡

5. **ምርምር ማለት፡-** በተፈጥሮ ሳይንስና የቴክኖሎጂ መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮችን ሲሆን በተለይም ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት በማላመድና በማሻሻል ላይ ያተኮረ የምርምር ዓይነት ነው

6. **ተቋማት ማለት፡-** የዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፤የኢንዱስትሪዎችና የምርምር ተቋማት የወል ስም ነው፡፡

7. **ሚኒስቴር ወይም ሚንስትር ማለት** ፡- ሚኒስቴር ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን ሚንስትር ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የበላይ ሃላፊ ማለት ነው፡፡

8. **ካውንስል ማለት**:- ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ማለት ነው

9. **ቴክኒክ ኮሚቴ ማለት፡-** በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ስር የሚደራጅ፤ በካውንስሉ የፀደቀውን ሀገራዊ የምርምር ቅደም ተከተል መሰረት አድርገው ለካውንስሉ ለድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክቶችን ገምግሞ ለውሳኔ ለካውንስሉ የሚያቀርብ ከተለያዩ የሙያ ዘርፎችና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙያ ማህበራት የተውጣጡ ባለሙያዎች አባል የሆኑበት ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

10. **የምርምር ድጋፍ ማለት፡-** ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ለሃገሪቱ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትርጉም ያለው አስተዋፅዎ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ለታመነበት የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን፤ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራን የሚገልበጥ፤ የማሻሻል፤ የማላመድ እና ወደ ምርትና አገልግሎት ለማስገባት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

11. **የምርምር ቡድን ማለት፡-** በአንድ ተቋም ውስጥ ወይም ሁለትና ከዚያ በላይ ከሆኑ ተቋማት የተውጣጡ ተመራማሪዎች በአንድ የምርምር ፕሮጀክት ላይ በጋራ

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
የሰው ሀብት ... ዳይሬክቶሬት አገልግሎት
አዲስ አበባ

ለመስራት የፈጠሩት ስብስብ ነው፡፡

12. ፕሮግራም ማለት፡-በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የሚደገፉ የረጅም ጊዜ የምርምር ተግባር ሲሆን በውስጡም ብዙ የምርምር ፕሮጀክቶችን የያዘና አጠቃላይ ግብና አላማ ያለው ነው፡፡

13.ፕሮጀክት ማለት፡- በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የሚደገፍ ምርምር ሃሳብ ሆኖ በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ የሚፈፀም የምርምር ተግባር ሲሆን በአላማና ግብ ተለይቶ የተቀመጠ ተግባርና የረሱ የሆነ በጀት ያለው ነው፡፡

14 **ፕሮፖዛል፡-**በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የሚደገፉ ምርምር ፕሮጀክቶች ላይ ለመሳተፍ ወይም ለመወደዳር የሚቀርብ የምርምር ፕሮጀክት መነሻ ዕቅድ ሲሆን አላማና ግብ፣ የተግበራት ጊዜ ሰሌዳና የገንዘብ መጠን የያዘ መነሻ ሰነድ ነው፡፡

15. ሴክተር ዘለል ማለት በአንድ ሴክተር ብቻ የማይፈፀም በብዙ ሴክተሮች የሚፈፀም ተግባር ነው፡፡

5. መርሆዎች

1. በካውንስሉ የሚደረገው የምርምር ድጋፍ በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡
2. ለድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክቶች በተቋማት የሚቀርቡ ወይም በቡድን የሚቀርቡ እና በተቋማት የሚደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. በተቻለ መጠን ለድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክቶች ሴክተር ዘለል(cross sectorial) የምርምር ፕሮጀክቶች መሆን አለባቸው፡፡

6. የምርምር ድጋፉ ዓላማ

1. ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች በሌሎች ሴክተሮች ሊደገፉ የማይችሉ ሀገራዊ ይዘት ያላቸውንና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም ከፍተኛ የሆኑ ትላልቅ ሴክተር

ዘለል(cross sectorial የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በውድድር ላይ በተመሰረተ አግባብ ለመደገፍ ነው፡፡

2. በሃገሪቱ ውስጥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎች በማጎልበት ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

ክፍል-ሁለት

የምርምር ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች መምረጫ መስፈርት

7. ስለ ምርምር ፕሮግራም ቅደም ተከተል አወጣጥ

1. ካውንስሉ ከተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት በመነሳት ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ቅደም ተከተል ያወጣል፡፡

2. የፕሮግራሞቹ መነሻ ሃሳብ ከዘርፍ የምርምር ካውንስሎች፤ ከሌሎች የምርምር ስራ ላይ ከሚሰሩ አካላት፤ ከመንግስት ወይም ከካውንስሉ ከራሱ የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3. የምርምር ፕሮግራሙ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ ሆኖ፤ ከቀረቡት የፕሮግራም መነሻ ሃሳቦች በመነሳት ካውንስሉ ቅደም ተከተል ለማውጣት የሚጠቅምባቸው መስፈርቶችም የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ይሆናሉ፡፡

ሀ/ ፕሮግራሙ ለሃገራዊ የልማት አቅዶችና ፕሮግራሞች ውጤታማነት ያለው ትርጉምና ፋይዳ፤

ለ/ ከፕሮግራሙ ውጤት የሚገኘው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም፤ በተለይም ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለምናደርገው ሽግግር ያለው ድርሻ፤

ሐ/ ፕሮግራሙ ለቀጣይ የሃገራችን የቴክኖሎጂ አቅም ክምችት የሚያበረክተው አስተዋፅዎ፤

መ/ ፕሮግራሙን ከሌሎች ሃገራዊ የልማት ፕሮግራሞች ጋር አስተሳስሮና አቀናጅቶ ለመምራት ያለው አመቺነት፤

ሠ/ ፕሮግራሙ ሌሎች ዘርፎችን ይዞ ለማደግ ያለው እምቅ አቅም፤

ረ/ ፕሮግራሙ ከአካባቢ ጥበቃና ከሃገራችን የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ልማት አቅጣጫ ጋር ያለው አግባብነት፤

ሰ/ ፕሮግራሙ ለዜጎች በተለይም ለሴቶች፤ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
የሬኮርድና ማህደር አገልግሎት
አዲስ አበባ

ክፍሎች ያለው አመቺነትና የሚሰጠው ጥቅም፤

ሸ/ ፕሮግራሙ እንደሁኔታው ከጎረቤቶቻችን ጋር በጋራ ጥቅም ላይ አብሮ ለመስራትና በጋራ ለመልማት የሚፈጥረው ምቹ ሁኔታ እና ሌሎችም ጉዳዮች ይሆናሉ::

4. ካውንስሉ ለእያንዳንዱ መስፈርት ክብደት በመስጠት የቀረቡትን መነሻ የፕሮግራም ሃሳቦች በዝርዝር ይገመግማል:: ለእያንዳንዳቸውም ነጥብ ይሰጣል::

5. የፕሮግራሞቹን ባለቤቶች ይለያል በግልጽ ይሰይማል፤ ዝርዝር የፕሮግራሙ ይዘት እንዲዘጋጅ ያደርጋል::

6. በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው የምርምር ፕሮግራሞች ከተለዩና ከፀደቁ በኋላ በእነዚህ ፕሮግራሞች ስር የሚካሄዱ የምርምር ፕሮጀክቶችንም ይለያል ይወስናል::

7. የፀደቁት የምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን አግባብ ባለው አካል ለሚመለከታቸው አካላት በስፋት የማስተዋወቅ ስራ መስራት ይኖርበታል::

8. ወቅቱን የጠበቀ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የወድድር ጥሪዎች በተለያዩ አግባቦች እንዲተላለፉ አቅጣጫዎችን ይሰጣል::

8. ለድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች የመምረጫ መስፈርት

ለድጋፍ የሚቀርቡት የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች የሚገመገሙት በሚከተሉት መስፈርቶች ይሆናል::

1/ የቀረበው የምርምር ፕሮጀክት ሃሳብ ከሃገራዊ የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫ ጋር ያለው ትስስር/ተዛምዶ

ሀ/ ከሃገሪቱ የምርምር የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መሆኑ፤

ለ/ የቀረበው የምርምር ፕሮጀክት ሃሳብ ከሌሎች የቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው የምርምር ፕሮጀክቶች ጋር ተጣጥሞ ለመሄድ ያለው አመቺነት፤

ሐ/ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ሴክተር ዘለል (cross-sectorial) ሀገራዊ ፋይዳ ያለው መሆኑ፤

አዲስ አበባ

8/ ለምርምር ቡድኑ አገልግሎት የሚሰጠው (host institute) ተቋማዊ አቅም

ለምርምር ቡድኑ አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም (host institute)

ሀ/ ለምርምር ቡድኑ የተፈቀደውን የምርምር ማካሄጃ ገንዘብ ህጋዊ በሆነ አሰራር ለመጠቀምና ወቅታዊ ፋይናንሺያል ሪፖርት ለማቅረብ መቻሉ፤

ለ/ ለምርምር ቡድኑ የምርምር ማካሄጃ የተሟላ ፋሲሊቲ (ዎርክ ሾፕ፤ ላቦራቶሪ ወዘተ) ያለው መሆኑ፤

9/ ምርምሩ በዩንቨርስቲ ኢንዱስትሪ ማዕቀፍ ውስጥ የሚሰራ መሆኑ

ሀ/ ምርምሩ ከተጨባጭ የኢንዱስትሪው ቴክኒካዊ ችግር የሚነሳ መሆኑ

ለ/ ከምርምር የሚገኘውን ውጤት ኢንዱስትሪው ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ፍላጎት ተነሳሽነትና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለምርምር ፕሮጀክቱ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ያሳየው ፍላጎት

9. ስለ ምርምር ካውንስሉ የውሳኔ አሰጣጥ ስነስርዓት

1/ በካውንስሉ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን የማፅደቅ እንደዚሁም በአግባቡ እየተከናወኑ አለመሆናቸው በተጨባጭ የተረጋገጡ ፕሮጀክቶችን በመገምገም የማቆም (የማቋረጥ) ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ካውንስሉ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ከአባላቱ ከ2/3 ኛ በላይ ተቀባይነት ሲያገኙ ነው፡፡

ክፍል- ሶስት

ቴክኒክ ኮሚቴ ስለማቋቋም

10. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴ መመስረት

1. ቴክኒክ ኮሚቴ ስለ መቋቋም

2/ የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ አዲስነት (Originality of the project)

ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ በሃገር ውስጥ ከዚህ ቀደም አሁን ለውድድር በቀረበው(ቡት) ተመራማሪ (ዎች) ወይም በሌሎች የተሰራ አለመሆኑ፤

3/ የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ጥራት

የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ለሳይንሳዊ ጥናት ምቹ የሆነና ምርምር ሊያስራ የሚችል መሆኑ፤

4/ የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ዕቅድ

ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ግልፅና ተያያዥነት ያለው የአሰራር ዕቅድና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማጠናቀቅ የሚቻልና የታቀደለትን ዓላማ የሚያሳካ መሆኑ፤

5. የተመራማሪው (ዎች) ብቃት

ለውድድር የቀረበውን የምርምር ፕሮጀክት ያቀረበው የተመራማሪዎች ቡድን ስብስብና የቡድኑ ጥንቅር ፕሮጀክቱን ከግብ ለማድረስ ወይም ለማጠናቀቅ ያላቸው ልምድና አቅም

6. የምርምር ፕሮጀክቱ ውጤት ለሃገር ዕድገት ያለው ጥቅም/ችግር ፈቺነት

ሀ/ የቀረበው የምርምር ፕሮጀክት ሃሳብ ውጤት ለመንግስት የልማት ፕሮግራም ውጤታማነት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ/ድርሻ

ለ/ የቀረበው የምርምር ፕሮጀክት ሃሳብ ውጤት በተጨባጭ የሚፈታው ችግር፤

7. የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ተአማኒነት

ሀ/ የፕሮጀክቱ ፕሮፖዛል ግልጽና አቀራረቡ የማያሻማ መሆንና የማከናወኛ ዘዴዎቹ በሳይንሳዊ ቀምር መርህ መሆናቸው፤

ለ/ የሚቀርበው የበጀት ጥያቄ ከቀረበው ፕሮጀክት ጋር ቀጥተኛና አግባብነት ያለው መሆኑ፤

ሐ/ የምርምር ስነምግባርን የተከተለ መሆኑ፤

አዲስ አበባ

ሀ/ በካውንስሉ የፀደቀውን ሃገራዊ የምርምር ቅደም ተከተል መሰረት አድርገው ለካውንስሉ ለድጋፍ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮጀክቶችን ገምግሞ ለውሳኔ ለካውንስሉ የሚያቀርብ ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች እና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙያ ማህበራት የተውጣጡ ባለሙያዎች አባል የሆኑበት የ ዘርፍ ባለሙያ ቴክኒክ ኮሚቴዎች በካውንስሉ ስር ይቋቋማል፡፡

ለ/ ቴክኒክ ኮሚቴው ከተለያዩ ሴክተሮች የሚቀርቡትን የምርምር ፕጀክት ፕሮፖዛሎች በአግባቡ ለመገምገም አቅም እንዲኖረው በሙያ ዘርፋቸው ስብጥር ላይ በተቻለ መጠን ቀረቤታ ያላቸው ቁጥራቸው እስከ 15 የሚሆኑ አባላት ይኖሩታል፡፡

ሐ/ ኮሚቴው የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ሆኖ፤ ስራ ዘመኑን የጨረሰው ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ እስከ ሶስት ጊዜ ድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

መ/ የኮሚቴ አባላቱ ምርጫ፤ በትምህርት ዝግጅት፤ በተማሩት የትምህርት ዘርፍ፤ በፕሮጀክት ግምገማና በምርምር ስራ ላይ ባላቸው ልምድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

ሠ/ ቴክኒክ ኮሚቴው በካውንስሉ የሚሰየሙ ስብሳቢና ፀሃፊ ይኖረዋል፡፡ሆኖም የፀሃፊነት ተግባር በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚቋቋመ ስራ ክፍል ድጋፍ ሚከናወኑ ይሆናል፡፡

ረ/ ቴክኒክ ኮሚቴው ስራ በሚሰረበት ጊዜ ለኮሚቴው አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በካውንስሉ ይወሰናል፡፡

2. የቴክኒክ ኮሚቴው አሰራር

ሀ/ ቴክኒክ ኮሚቴው በየሶስት ወሩ በመደበኛነት እየተገናኘ የተደገፉ የምርምር ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይገመግማል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ በሰብሳቢው በሚደረገው ጥሪ መሰረት እየተገናኘ ስራውን ያከናውናል፡፡

ለ/ የቴክኒክ ኮሚቴው የስራ ቦታ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መ/ቤት ሆኖ ኮሚቴው ስራ በሚሰረበት ጊዜ ሁሉ የሚያስፈልገው ወጪ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ሐ/ በቴክኒክ ኮሚቴው የሚወሰኑ ጉዳዮች በተቻለ መጠን በመግባባት ላይ የተመሰረተ ሆኖ መተማመን ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ከነልዩነት ሃሳቦቹ ለመጨረሻ ውሳኔ ለካውንስሉ ይቀርባሉ፡፡ ካውንስሉ ጉዳዩን ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3. የቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት

ሀ/ ቴክኒክ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 ላይ የተመለከቱትን በስፈርቶች መነሻ በማድረግ ካውንስሉ በሚያደረገው ጥሪ መሰረት ለውድድር የሚቀርቡለትን የምርምር ፕሮጀክቶች የሚገመግምበት ዝርዝር መስፈርት ያዘጋጃል፡፡ በካውንስሉ ያስፀድቃል፡፡

ለ/ በፀደቀው ዝርዝር መስፈርት መሰረት የቀረቡለትን የምርምር ፕሮጀክቶች በመገምገም በቅደም ተከተል ለድጋፍ ለካውንስሉ የመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡

ሐ/ የተደገፉት የምርምር ፕሮጀክቶች በዕቅዳቸውና በውል ስምምነት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት የቴክኒክና ፋይናንሺያል ሪፖርታቸውን አፈፃፀም ይገመግማል፡፡

መ/እንደአስፈላጊነቱ በአካል ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱበት ቦታ በመገኘት የመስክ ምልከታ ፣ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፡፡

ሠ/ ከምርምር ፕሮጀክት ግምገማ ጋር በተያያዘ ስላከናወናቸው ተግባራት በየስስት ወሩ ለካውንስሉ የፁሁፍ ሪፖርት ያቀርባል

ክፍል- አራት

የምርምር ድጋፍ አሰጣጥና ተጓዳኝ ተግባራት

11. የምርምር ድጋፍ ፕሮግራሙ ሽፋን

1. በሌሎች ሴክተሮች ሊደገፉ የማይችሉ ሀገራዊ ይዘት ያላቸውንና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም ከፍተኛ የሆኑ ትላልቅ ሴክተር ዘለል (cross sectorial) ፕሮጀክቶች ለካውንስሉ እየቀረቡ ይገመገማሉ፤ በውድድር ላይ በተመሰረተ አግባብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

2. ለዚህም ካውንስሉ በድጋፉ መጠቀም ለሚችሉ የምርምር ቡድኖችና ተቋማት በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያዎች አግባብነት ባለው መጠን ጥሪ (Call for Paper) ያደርጋል፡፡

3. በጥሪው መሰረት የቀረቡ የምርምር ሃሳቦች ተወዳድረው በመስፈርቱ መሰረት ብልጫ ያገኙትና የተመረጡት የምርምር ሃሳቦች የገንዘብ ድጋፉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

4. በካውንስሉ የሚደረገው የምርምር ድጋፍ ቀደም ሲል በወጣው የምርምር ቅደም ተከተልና በመንግስት የልማት ፕሮግራሞች ላይ ያተኮረ ሆኖ ዋነኛ ትኩረቱም፡-

   ሀ/ በግብርና

   ለ/ በኢንዱስትሪ

   ሐ/ በጤና

   መ/ በማዕድንና ውሃ

   ሠ/ በኮንስትራክሽን

   ረ/ በኢንፎርሜን ኮሙኒኬሽን

   ሰ/ በኢነርጂ

   ሸ/ በአካባቢ ጥበቃ እና ተዛማጅ ዘርፎች ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ድጋፍ የሚሸፈኑት የምርምር ፕሮጀክቶች ዕድሜ እንደፕሮጀክቶቹ ባህሪ፤ ይዘትና ስፋት የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛው የፕሮጀክቱ ዕድሜ እስከ ሶስት ዓመት ሊሆን ይችላል፡፡

12. በድጋፉ ለመጠቀም የሚችሉ አካላት

1/ የድጋፉ ተጠቃሚዎችም በተጠቀሱት ዘርፎች ፕጀክት ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ምርምር ለማካሄድ የሚያቀርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ እውቅና አግኝተው የተቋቋሙ /የተደረጁ እና የምርምር ተግበራትን የሚያከናወኑ ተቋማት ሊሆኑ ይችላላ፡፡

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ... የፈጠራ ... አገልግሎት

2/ በተለይም የምርምር ቡድኑ መሪ (Principal Investigator) ኢትዮጵያዊ መሆን ያለበት ሲሆን ነገር ግን በቡድኑ ውስጥ የሌሎች ሃገሮች ዜጎች (Co-researcher) የሚሳተፉበት ዕድል ሊኖር ይችላል።

13. ለተመረጡ አመልካቾች የማሳወቂያ ዘዴና አካሄድ

በካውንስሉ አማካኝነት በአሸናፊነት የተመረጡ ፕሮፖዛሎችን ማፅደቅ ስራ እንደተጠናቀቀ

1. በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በኩል አሸናፊዎች፣ በደብዳቤ፣ በኢሜይልና በስልክ ውጤቱን እንዲያውቁት ይደረጋል።
2. ያልተመረጡ ወይም ፕሮፖዛላቸው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካቾችም በተመሳሳይ አግባብ እንዲያውቁት ይደረጋል።

14. የድጋፍ ስምምነት ውል ስለመፈፀም

የስምምነት መፈራረሚያ ሰነድ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚዘጋጅ ሲሆን አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ይሆናል።

1. የስምምነቱ መፈራረሚያ ሰነድ ይፋ በሆነ ስነስርዓት ሁሉም ወገኖች በተገኙበት ይካሄዳል።

2. በፊርማ ስነስርዓቱ ላይ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚንስትር ካውንስሉን በመወከል፣ የምርምር ፕሮፖዛሉ ተቀባይነት ያገኘው የምርምር ቡድን/የተቋም ሃላፊ፣ እና ለተመራማሪው አገልግሎት የሚሰጠው (host institute) ተገኝተው ስምምነቱን ይፈርማሉ።

3. የስምምነት ፊርማ ከተጠናቀቀ በኋላ ህጋዊ ማህተም አርፎበት የስምምነት ኮፒዎች ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ ለምርምር ቡድኑ እና ተመራማሪው ለሚሰራበት ተቋም (host institute) ይሰጣል።

15. የምርምር ድጋፍ ክፍያ ስርዓትና የድጋፍ መጠን

1. ካውንስሉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለሚያደርጋቸው የምርምር ድጋፎች የሚውለው ገንዘብ በየዓመቱ ከመንግስት የሚመደብ በጀት ሲሆን፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

ካውንስሉን በመወከል የበጀት ጥያቄውን የዓመቱን የበጀት ዑደት ተከትሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመጠየቅ ያስፈቅዳል፡፡

2. የሚንስቴር መሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬትም የፋይናንስ ደንብና መመሪያን ተከትሎ በካውንስሉ ውሳኔ መሰረት የገንዘብ እንቅስቃሴውን ይከታተላል፤ ያስተዳድራል፡፡

3. ካውንስሉ አወዳድሮ የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን እንደ ፕሮጀክቱ ሃገራዊ ጠቀሜታ፤ ስፋትና ጥበት እየታየ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ለምርምር ድጋፉ የሚሰጠው ከፍተኛ የበጀት ጣሪያም ብር 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን ብር) ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ የገንዘብ ድጋፍ መጠን እንደ ወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም እየታየ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

4. ለምርምሩ የሚውለው የገንዘብ ድጋፍ የሚፈፀመው በካውንስሉ አሰራር መመሪያ መሰረት ሲሆን አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

5. የድጋፉ የመጀመሪያው ክፍያ የድጋፉ ስምምነት ፊርማ በተፈረመ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የሚፈፀም ሆኖ የድጋፉ አከፋፈል መጠን ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው የምርምር ድጋፍ የበጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የውስጥ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

6. ከመጀመሪያው ዙር ክፍያ በኋላ የሚኖረው የድጋፍ ገንዘብ አከፋፈል ተፈፃሚ የሚሆነው ስለ ፕሮጀክቱ ክንውን የሚቀርበውን የቴክኒክ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት በመገምገምና እንደአስፈላጊነቱም በመስክ ተገኝቶ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የደረሰበትን ደረጃ በመመልከት ይሆናል፡፡

7. የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ጥቅም ላይ የሚውለው በፕሮጀክቱ ፕሮፖዛል ላይ ለተመለከቱትና ለፀደቁት የፕሮጀክቱ የወጪ ርዕሶች ብቻ ነው፡፡

16. የድጋፉን ቀሪ ገንዘብ ስለመመለስ

ድጋፉን የተቀበለው የምርምር ቡድን ወይም ድርጅት በስምምነት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የፕሮጀክቱ ስራ እንደተጠናቀቀ ወጪውን ኦዲት በማስደረግ መመለስ የሚገባው ቀሪ ገንዘብ ካለ በሶስት ወር ጊዜ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

17. ከድጋፍ መውጣት

ለምርምር የገንዘብ ድጋፍ የጠየቀ የምርምር ቡድን በተለያዩ ምክንያቶች የጠየቀውን ወይም የጀመረውን የምርምር ስራ ለማቋረጥ ከፈለገ/ከተገደደ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በደብዳቤ በማሳወቅ ከድጋፉ መውጣት ይችላል፡፡ ነገር ግን የምርምር ቡድኑ የስምምነት ፊርማ ከተፈረመና የድጋፍ ገንዘብ ከተረከበ በኋላ ስራ ለማቆም ከፈለገ /ከተገደደ የወሰደውን ገንዘብ ወዲያውኑ መመለስ አለበት፡፡

18.የምርምር ፕሮጀክት ትግበራ ክትትልና ግምገማ

በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል አማካኝነት ድጋፍ የሚሰጣቸው የምርምር ፕሮጀክቶች በሙሉ መተግበር ያለባቸው ለድጋፍ ቀርቦ በፀደቀው ዋና ፕሮፖዛልና በተፈረመው የድጋፍ ስምምነት አንፃር ብቻ ይሆናል፡፡ የፕሮጀክቱ ትግበራ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ እየተተገበረ ወይም እየተሰራ መሆኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በቴክኒክ ኮሚቴውና ይህን ስራ እንዲከታተል በተሰየመው የስራ ክፍል አማካኝነት ክትትልና ቁጥጥር ያደረጋል፡፡

19. የፕሮጀክት አፈፃጸም ሪፖርት

የፕሮጀክቱ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት የገንዘብ ደጋፉ ከተሠጠ ቀን ጀምሮ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅበት ወቅት ድረስ የፕሮጀክት አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይህን ጉዳይ እንዲከታተል ለተሰየመው የስራ ክፍል መቅረብ አለበት፡፡ ሪፖርቱ ካልቀረበ በቀጣይ መከፈል የሚገባው የድጋፍ ክፍያ አይከናወንም፡፡

20. የአፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ

የአፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ አጠቃላይ የሚደረገው የምርምር ፕሮጀክቱ የወደፊት አካሄድና አቅጣጫ እንዲሁም የድጋፉ አከፋፋል እንዴት መሆን እንዳበት ለመወሰን ነው ፡፡ የሪፖርቱ ግምገማ የሚከናወነው በቴክኒክ ኮሚቴው አማካኝነት አፈፃፀሙ ከፕሮጀክቱ ዕቅድና መርሃግብር ጋር በማነፃፀር ይሆናል ፡፡ በቀጣይነትም ኮሚቴው የቀረበውን የአፈፃፀም ሪፖርት በመገምገምና በማጠናቀር ከውሳኔ ከአስተያየት ጋር ለካውንስሉ ያቀርባል፡፡

21. የፕሮጀክቱ አፈፃጸም የማጠቃለያ ሪፖርት

የምርምር ፕሮጀክቱ የማጠቃለያ ሪፖርት የፋይናንስ ሪፖርትን ጨምሮ ፕሮጀክቱ በተጠናቀቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ፕሮጀክቱን በበላይነት ከሚመራው ተቋም (Host Institution) ተረጋግጦ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

22. የምርምር ውጤት ግምገማ

የምርምር ውጤት ግምገማ የፕሮጀክቱ ማጠቃለያ ሪፖርት ግምገማ ሲሆን ይህም በቴክኒክ ኮሚቴ አባላትና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች በዘርፉ የካበት ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በመጋበዝ እንደዚሁም የውጤቱ ተጠቃሚዎች በተገኙበት ለአውደ ጥናት በማቅረብ ግምገማ ይደረግበታል፡፡

22. ድጋፍ ማቆም ወይም ማቋረጥ (Termination of Funding Report)

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ቴክኒክ ኮሚቴውን በመጠቀም ፕሮጀክቱን በአካል በመገምገምና በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት የፕሮጀክቱን አካሄድ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘ ድጋፉን በማቋረጥና የተሰጠውን የድጋፍ ገንዘብ በፕሮጀክቱ ላይ ከተጠቀሰው ዓላማ ውጪ ውሎ ቢገኝ ለባከነው ገንዘብ የሚመለከተው ተመራማሪ ወይም ተቋም/ ክፍል በገባው ስምምነት መሰረት በህግ ተጠያቂ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ውጤቱንም ለካውንስሉ ያሳውቃል፡፡

23 . የምርምር ድጋፉ የበጀት ምንጮች

ሀ/ መንግስት ለብሄራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል
ዓመታዊ ለምርምር ድጋፍ የሚመደብ መደበኛ በጀት

ለ/ ከግሉ ሴክር ፣ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶችና ምርምር ተቋማት ከሚገኝ ምርምር ድጋፍ

24. ያለተጨማሪ የበጀት ጥያቄ የጊዜ ማራዘሚያ ስለመጠየቅ

በካውንስሉ ድጋፍ የተደረገላቸው የምርምር ፕሮጀክቶች በተቻለ መጠን በዕቅዱ ላይ በተቀመጠው ጊዜ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተደገፉ ፕሮጀክቶች በዕቅዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መጠናቀቅ ካልቻሉና ለዚህም አሳማኝ በሆነ ምክንያት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ በምርምር ቡድኑ ከቀረበ የጥያቄው አስፈላጊነትና አግባብነት በካውንስሉ ታይቶ ከታመነበት ያለተጨማሪ በጀት የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደሁኔታው ከ6 ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

25.ድጋሚ ስለማመልከት (Resubmission)

1. ለድጋፍ ለውድድር የቀረበ ምርምር ፕሮጀክት ዋና ዋና መመዘኛዎችን የሚያሟሉና በይዘታቸውም ተመራጭ ሆነው ነገር ግን ጥቂትም ቢሆን በተሟላ መልኩ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ካሉ በቴክኒክ ኮሚቴው ግብረ መልስ ተሰጥቷቸው እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡
2. ነገር ግን በዚህ አግባብ የማይስተካከሉ ሆነው ከዚህ በፊት ተቀባይነት ያላገኘ የምርምር ፕሮጀክት በድጋሚ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው መሻሻል የሚገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ተስተካክለው መቅረባቸው መረጃ ሲቀርብና የጥናት ቡድኑ ቀድሞ አቅርቦ የነበረውንና የተሻሻለውን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በንጽጽር ፤በዝርዝርና በግልፅ ፁሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ተስተካክሎ በድጋሚ የቀረበው ፕሮፖዛል እንደ አዲስ እንዲታይና እንዲገመገም ይደረጋል፡፡

ክፍል-አምስት

ከምርምር ድጋፍ ስርዓት ተዋናዮች የሚጠበቁ ሃላፊነቶች

26. ከብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል የሚጠበቅ

1. ከተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት በመነሳት ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ቅደም ተከተል ማውጣት፤
2. በፀደቁ ፕሮግራሞች ስር የሚካሄዱ የምርምር ፕሮጀክቶችን መለየትና መወሰን፤
3. ለተመራማሪዎችና ተቋማት በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያዎች አግባብነት ባለው መጠን ጥሪ (Call for Paper)ማድረግ፤
4. በሌሎች ሴክተሮች ሊደገፉ የማይችሉ ሀገራዊ ይዘት ያላቸውንና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም ከፍተኛ የሆኑ ትላልቅ ሁሉ አቀፍ ዘርፍ የምርምር ፕሮጀክቶች አወዳድሮ መደገፍ፤
5. ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች እና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙያ ማህበራት የተውጣጡ ባለሙያዎች አባል የሆኑበት የዘርፍ ባለሙያ ቴክኒክ ኮሚቴዎች በካውንስሉ ስር ማቋቋም፤
6. የቴክኒክ ኮሚቴውን ስብሳቢና ፀሃፊ መሰየም፡፡
7. ቴክኒክ ኮሚቴው ስራ በሚሰረበት ጊዜ ለኮሚቴው አባላት የሚከፈለው አበል መጠን መወሰን፡፡

8. በቴክኒክ ኮሚቴው የሚዘጋጀውን ዝርዝር መስፈርት ማፅደቅ፡፡

27. ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚጠበቅ

1. ለድጋፍ ተወዳድረው በካውንስሉ ለተመረጡ አሸናፊዎች፤ በደብዳቤ፤ በኢሜይልና በስልክ ውጤቱን እንዲያውቁት ማድረግ፡፡

2. ያልተመረጡ ወይም ፕሮፖዛላቸው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካቾችም በተመሳሳይ አግባብ እንዲያውቁት ማድረግ፡፡

3. የስምምነት መፈራረሚያ ሰነድ ማዘጋጀት፤ ካውንስሉን በመወከል ከአሸናፊ ተመራማሪዎች እና ለተመራማሪዎች አገልግሎት ከሚሰጡ (host institutes) ጋር ስምምነቱን መፈረም፡፡

4. የስምምነቱን ኮፒ ፋይል አድርጎ መያዝ፤መጠበቅ፤

5. የመንግስት የፋይናንስ ደንብና መመሪያን እንደዚሁም የካውንስሉን የምርምር ድጋፍ በጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የውስጥ መመሪያ ተከትሎ በካውንስሉ ውሳኔ መሰረት ለተደገፉ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ክፍያ መፈፀም እንቅስቃሴውን መከታተልና፤ለዚሁ ተግባር የተመደበውን በጀት ማስተዳደር፤

6. ቴክኒክ ኮሚቴውን በመጠቀም በካውንስሉ የተደገፉ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በአካል ተገኝቶ መገምገምና ለካውንስሉ ሪፖርት ማቅረብ፤

7. የቴክኒክ ኮሚቴው ስራ በሚሰረበት ጊዜ ሁሉ የሚያስፈልገውን ወጪ በካውንስሉ የበጀት አጠቃቀምና አስተዳደር የውስጥ መመሪያ መሰረት መሸፈን፤

28. ከሌሎች የምርምር ካውንስሉ አባል የሆኑ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የሚጠበቅ

1. በካውንስሉ የፀደቁ የምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ለሚመለከታቸው አካላት በስፋት ማስተዋወቅ፤
2. በየሚመሯቸው ዘርፎች ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው ሁሉ አቀፍ ዘርፍ የምርምር ፕሮጀክቶች እንዲቀርቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

ክፍል - ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29. የፈጠራና የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ

ካውንስሉ ድጋፍ ለሰጣቸው የምርምር ፕሮጀክቶች የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ግኝቶች ወይም ውጤቶች ጉዳዩን በማጥናት ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመሆን የባለቤትነት መብት እንዲጠበቅ ያስደርጋል፡፡

30. ምስጋናና ዕውቅና ስለመስጠት

በብሄራዊ ካውንስሉ በሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት የተገኘ የምርምር ውጤት በፁሁፍ፤ በቪዲዮ፤ በጆርናል፤ ወይም በየትኛውም ዓይነት የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መልክ ሲታተምና ወደ ኢንዱስትሪ ገብቶ ምርቱ ገበያ ላይ ሲወጣ በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ካውንስል ድጋፍ መሆኑን የሚገልፅ ወይም እውቅና የሚሰጥ ፁሁፍ በግልፅ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

31. የህግ ጉዳይ (Legal Issue)

ከምርምር ድጋፉ ስምምነት ጋር ተያያዥነት ኖሯቸው የሚነሱ የህግ ጉዳዮች በሃገሪቱ ህግ መሰረት የሚታዩ ይሆናሉ፡፡

32. መመሪያውን ስለማሻሻል

የምርምር ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያውን ካውንስሉ ባመነበት ጊዜ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡

33. የድጋፍ መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ የምርምር ድጋፍ መመሪያ ከጥቅምት/ 2007 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ደሚቱ ሃምቢሳ

ሚንስትር

ጥቅምት 2007 ዓ/ም
አዲስ አበባ